የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

10ኛ ዓመት ቁጥር 5
10th year No 5

ሐረር ጥቅምት 24 ቀን 1997 ዓ.ም
HARAR November. 3 . 2004

| ያንዱ ዋጋ ብር 2<br>Unit Price Br. 2 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box |
|---|---|---|


ማውጫ


ደንብ ቁጥር 8/1997ዓ.ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የቀበሌ አካባቢ መስተዳድር ምክር ቤቶችን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ የመስተዳድር ም/ቤት ደንብ ——ገጽ 398


## ደንብ ቁጥር 8/1997 በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የቀበሌ አካባቢ መስተዳደር ምክር ቤቶችን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ

በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የተቋቋሙት አስፈጻሚ አካላት በህግ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ለመተግበር እንዲችሉ የሥራ ዘርፎቻቸውን ወደ ህዝቡ በማውረድና በማደራጀት የህዝቡን አሳታፊነት በየደረጃው በማረጋገጥ በአቅራቢያው አገልግሎቶች እንዲያገኝ ማድረግ በማስፈለጉ::

የመንግስት የሥራ ዘርፎችን ወደ ህዝቡ ለማውረድ እንዲቻል በአዋጅ ቁጥር 44/96 መሠረት የተቋቋሙትን የቀበሌ አስተዳደር አካላት ልማት ለማምጣት ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት አስኪቃኙ ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ ሆኖ አዲስ በሚዋቀሩት የቀበሌ አካባቢ መስተዳድር ምክር ቤቶች እየተጣመሩ የሚመሩበትን ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ::

የክልሉን መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 28 እና 32 መሠረት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል::

## ምዕራፍ አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ:

ይህ ደንብ " በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤቶችን አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን የወጣ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 8 /1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ:

የቃሉ-አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

ሀ/ «የክልል መስተዳድር ምክር ቤት» ማለት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 60 መሠረት በክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ስልጣን የተሰጠው አካል ነው::

ለ/ « መማክርት ጉባኤ ማለት » በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 መሠረት የተቋቋመ ጊዜያዊ ምክር ቤት ነው::

ሐ/ "የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት በታችኛው የእርከን ደረጃ የሚገኙ በአዋጅ ቁጥር 44/96 የተቋቋሙበትን ከአንድ በላይ የሆኑ የቀበሌ አስተዳደሮች በማማከል በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ የከተማና የገጠር ቀበሌ አካባቢ ህግ አስፈጻሚ አካል ነው::

መ/ «ንዑስ ቀበሌ » ማለት በአዋጅ ቁጥር 44/96 መሠረት የተቋቋመ የቀበሌ አስተዳደር ማለት ነው

### 3. ዓላማ:

የዚህ ደንብ ዓላማ በአዲሱ የክልሉ መንግስት አወቃቀር መሠረት በቀበሌ አካባቢ ደረጃ ህዝቡን በየልማት መስኩ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ መልካም አስተዳደርና ፈጣን ልማት እንዲሰፍን እና የቀልጣፋ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል አቅም መፍጠር ነው::

### 4. ስለ ቀበሌ መስተዳድር አደረጃጀት

1- በክልሉ ህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ የተፋጠነ ልማት ሊያስመዘግብ የሚችል የነዋሪውን ህዝብ ቁጥር ያማከለና ህገ-መንግስታዊ እውቅና ያለውን የመጨረሻውን መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ማቋቋም ይቻል ዘንድ በክልሉ እየተሰራበት ያለው 36 (ሰላሳ ስድስት) የከተማና የገጠር ቀበሌ የሥልጣን ክልል በዚህ ደንብ መሠረት በ6 (ስድስት) የከተማና በ3(ሦስት) የገጠር ቀበሌ አካባቢ የሥልጣን ወሰን ክልል ይደራጃሉ::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 በተመለከተው መሠረት የ9ኙ የቀበሌ አካባቢዎች የሥልጣን አደረጃጀት እና ስያሜ ከዚህ በታች የተመለከተው ይሆናል::

ሀ- አሚር ኑር አካባቢ ቀበሌ የከተማ ንዑስ ቀበሌዎች
(1) ቀበሌ 01
(2) ቀበሌ 02 እና
(3) » 07 ክልልን ያካትታል::

ለ- አባዲር አካባቢ ቀበሌ የከተማ ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) ቀበሌ 03
(2) » 04
(3) » 05 እና
(4) » 06 ክልልን ያካትታል::

ሐ- ሸንኮር አካባቢ ቀበሌ የከተማ ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) ቀበሌ 08
(2) ቀበሌ 09 እና
(3) ቀበሌ 10 ክልልን ያካትታል::

መ- አቦከር አካባቢ ቀበሌ የከተማ ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) ቀበሌ 11
(2) ቀበሌ 12 እና
(3) ቀበሌ 13 ክልልን ያካትታል::

ሠ- ጅንኢላ አካባቢ ቀበሌ የከተማ ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) ቀበሌ 14
(2) ቀበሌ 15 እና
(3) ቀበሌ 16 ክልልን ያካትታል::

ረ- ሐኪም አካባቢ የከተማ ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) ቀበሌ 17
(2) ቀበሌ 18 እና
(3) ቀበሌ 19 ክልልን ያካትታል::

ሰ- ኤረር አካባቢ ቀበሌ የገጠር ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) ኤረር ወልድያ ቀበሌ
(2) ኤረር ዶዶታ ቀበሌ
(3) ሀዋዌ ቀበሌ እና
(4) ኡሳን ኡሳ ቀበሌ ክልልን ያካትታል::

ሸ- ድሬ-ጠያራ አካባቢ ቀበሌ የገጠር ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም:-
(1) አቦከር ሙጢ ቀበሌ
(2) ድሬጠያራ ቀበሌ
(3) ስገቻ ቀበሌ
(4) ሐሰንጌይ ቀበሌ
(5) ሚያይ ቀበሌ እና
(6) ሱቁል ቀበሌ ክልልን ያካትታል::

ቀ- ሶፊ አካባቢ ቀበሌ የገጠር ንዑስ ቀበሌዎች ማለትም :-
(1) ገልመሸራ ቀበሌ
(2) አውበርኸድሌ ቀበሌ
(3) ሶፊ ቀበሌ
(4) ቡርቃ ቀበሌ
(5) ሐረዋ ቀበሌ
(6) አው አመር ቀበሌና
(7) ቂሌ ቀበሌ ክልልን ያካትታል::

3. በዚህ ደንብ መሠረት የተደራጁ የቀበሌ መስተዳድሮች ስያሜን በተመለከተ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እንዳስፈላጊነቱ መመሪያ ሲያወጣ ይችላል::

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለ ቀበሌ መስተዳድር አደረጃጀትና ሥልጣን

### 5. ስለ ቀበሌ መስተዳድር አደረጃጀትና ተጠሪነት:

1. የቀበሌ መስተዳድር የክልሉ የመጨረሻው መንግስታዊ የመስተዳድር እርከን ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት /ካቢኔ/ ነው::
2. የቀበሌ መስተዳድር የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል:
   ሀ. የቀበሌ መማክርት ጉባኤ
   ለ. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት(የቀበሌ ካቢኔ)

## ክፍል አንድ
## ስለ ቀበሌ መማክርት ጉባኤ

### 6. ስለ ቀበሌ መማክርት ጉባኤ መቋቋም

የቀበሌ መስተዳድር ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሆነው የቀበሌ ምክር ቤት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እስኪቋቋም ድረስ ተከተ የሚሰራ የቀበሌ መማክርት ጉባኤ በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ ሆኖ :-

1- ከቀበሌው ነዋሪ ህዝብ የሚወከሉ አባላት ያሉት አማካሪ ምክር ቤት ነው:
2- የጉባኤ ሰብሳቢና ፡ ምክትል ሰብሳቢ እንዲሁም:-
3- እንደአስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይኖሩታል::

### 7. ስለ ቀበሌ መማክርት ጉባኤ አባላት እና አመራር አመራረጥ

1- የመማክርት ጉባኤ አበላት በቀጥታ ከህዝቡ የሚወከሉ ሆኖ በየቀበሌው ሥር በተዋቀሩት እያንዳንዱ ንዑስ ቀበሌ ከሚገኙ የሁሉም ህብረተሰብ ክፍሎች መካከል በቀጥታ ይመረጣሉ፣ዝርዝሩ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት / ካቢኔ/ /መመሪያ ይወሰናል::
2- የመማክርት ጉባኤዎች ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ከጉባኤ አባላት መካከል በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይሰየማሉ

### 8. የቀበሌ መማክርት ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1- የፌደራልና የክልሉ መንግስት ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል::
2- የቀበሌውን ኢኮኖሚያዊ ልማት ማህበራዊ አገልግሎቶችንና አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ረቂቅ ዕቅድ ይገመግማል: በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል:
3- ነዋሪው ህዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል:
4- የቀበሌው መስተዳድር ምክር ቤት የልማት አጋዥ ኃይል በመሆን ይንቀሳቀሳል:
5- ስሥራው መቃናት እንዲያግዙ ልዩልዩ ኮሚቴዎችን እንደስፈላጊነቱ ያደራጃል:ሥራዎቻቸውንም በቅርበት ይከታተላል ይገመግማል
6- የቀበሌውን መስተዳድር ምክር ቤት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያዳምጣል ይገመግማል:የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል
7- ስለ አከናወናቸው ተግባራት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል:

### 9. ስለ ቀበሌ መማክርት ጉባኤ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ:

1- የመማክርት ጉባኤ ሰብሳቢ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚሰየም ሆኖ:-
   (ሀ) አማካሪ ምክር ቤቱን ይሰበስባል ይመራል
   (ለ) አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል
   (ሐ) ቃለ-ጉባኤና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል ይቆጣጠራል
   (መ) የመማክርት ጉባኤውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል
   (ሠ) ጉባኤው የሚሰጠውን ሌሎች ጉዳዮች ያከናውናል
2- የመማክርት ጉባኤው ምክትል ሰብሳቢም በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ2 መሠረት እንዲሁ የሚሰየም ሆኖ:-
   (ሀ) በሰብሳቢው ተሰይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል
   (ለ) ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተከተ ይሠራል::

### 10. የመማክርት ጉባኤ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1- የመማክርት ጉባኤ መደበኛ ስብሰባውን በየሦስት ወር አንዴ ይካሄዳል
2- ከአባላቱ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተ-ጉባኤ ይሆናል ውሳኔ የሚተላለፈውም በአብላጫ ድምፅ ይሆናል:
3- የመማክርት ጉባኤው የሥራ ዘመን የሚያበቃው አግባብ ባለው ህግ መሠረት የቀበሌ ምክር ቤቶች ምርጫ ተካሄዶ በውጤቱ መሠረት አዲስ ምክር ቤት ሥራውን ሲጀምር ይሆናል::

## ክፍል ሁለት
## ስለ ቀበሌ አካባቢ ህግ አስፈፃሚ አካል

### 11. የቀበሌው መስተዳድር ምክር ቤት መቋቋም

የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 ከንዑስ አንቀጽ1 (ሐ) ) የተዘረዘሩት በያንዳንዱ ቀበሌ የሚቋቋሙ የማኅበራዊና አገልግሎት ሰጭ የመንግስት ተቋማት አስተባባሪዎችና አስፈላጊ ሠራተኞች የሚገኙበትና የበላይ በሆኑት የመስተዳድር አካላት ለሚወጡ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች የበታች አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ መሠረት ተቋቁሟል::

### 12. ስለ ቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነት

የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት የቀበሌ አካባቢ የህግ አስፈጻሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለቀበሌው መማክርት ጉባኤ ወይም ለተተኪው አካልና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል::

### 13. ስለ ቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1- የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-
   ሀ/ የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ
   ለ/ የቀበሌ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ
   ሐ/ የቀበሌ ትምህርትና አቅም ግንባታ አስተባባሪ
   መ/ የቀበሌ ሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ አስተባባሪ
   ሠ/ የቀበሌ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት አስተባባሪ
   ረ/ የቀበሌ ጤና አስተባባሪ
   ሰ/ የቀበሌ የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት አስተባባሪ (በከተማ)
   ሸ/ የቀበሌ ግብርና፣ ገጠር ልማትና የምግብ ዋስትና አስተባባሪ (በገጠር)
   ቀ/ የቀበሌ የማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት አስተባባሪ
   በ/ የቀበሌ የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ አስተባባሪ
   ተ/ የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ (በከተማ)

2- የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌውን መስተዳደር ሥራ ይመራሉ ያስተባብራሉ:

3- የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በምክር ቤቱ አባልነታቸው ለሚሰጡት ውሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው::

### 14 .የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፤

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባሬት ይኖሩታል::
   ሀ/ ቀበሌ የልማትና የነዋሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ ማዕከል በመሆኑና በቀበሌ ደረጃ ሊሰጡ ለሚችሉ አገልግሎቶች ጣቢያ ሆኖ የቀበሌው ነዋሪዎችን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለልማት ያነሳሳል:
   ለ/ የአካባቢ ልማት ሥራዎች የከተማውን ፕላን፣የግንባታ ህጎችና ደረጃዎች ጠብቀው መሰራታቸውን ይከታተላል ፤ ህገ-ወጥ ግንባታምንም ይቆጣጠራል፤ በህግ መሠረት ይከላከላል፤
   ሐ/ በቀበሌው የሥነ-ሥርዓት አስከባሪዎችን ያሰማራል:የሚያከናውኑትን ሥራ ይቆጣጠራል በቀበሌው ክልል ውስጥ ህገ-ወጥ ድርጊቶች እንዳይካሄዱ ይከታተላል:ይቆጣጠራል
   መ/ የቀበሌው ነዋሪ ህብረተሰብ የአካባቢውን ጽዳት እንዲጠበቅ እና እንዲያስውብ ያስተባብራል:ይቆጣጠራል
   ሠ/ የቀበሌው ነዋሪዎች ተሳትፎ ለማጎልበት እንዲረዳ የተለያዩ ብዙሃን ማህበራትና ማህበራዊ ተቋማት እንዲደራጁና ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የሙያና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል ያስተባብራል:
   ረ/ በአነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ሥራዎች በዕደ-ጥበብ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማህበር እንዲደራጁ ያበረታታል:ተገቢውን ድጋፍ የሚያገኙ ብትን ሁኔታ ያመቻቻል አሠራራቸውንም ይከታተላል:ይቆጣጠራል:
   ሰ/ ጎጂ ባህሎችን ለማስወገድ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል የበሽታ መከላከልና የመሠረተ ጤና ትምህርትንና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ ለነዋሪው ሕብረተሰብ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ይከታተላል በቀበሌ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል ለሚንቀሳቀሱ ተቋማት ድጋፍ ይሰጣል:
   ሸ/ የቀበሌውን አጠቃላይ ዕቅዶች መርሀ-ግብሮችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤አፈጻጸማቸውን ይከታተላል:
   ቀ/ ፖሊሲዎች ህጎች ደረጃዎችና የአስተዳደሩ የበላይ አካላት ውሳኔዎች በቀበሌው ተግባራዊ መሆናቸውንና የቀበሌው ፀጥታ መጠበቁን ያረጋግጣል፤
   በ/ የቀበሌውን አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ሥራ ይመራል ያስተባብራል ለቀበሌው ሠራተኞች ሥልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በቀበሌው ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፤
   ተ/ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ የአጸደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይከታተላል የመሠረተ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል:
   ቸ/ የተፈቀደለትን በጀት ይደለድላል በሥራ ላይ ያውላል የተሟላ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል አፈጻጸሙ በፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሠረት መሆኑን ይከታተላል የደረጃ «ሐ» ግብር ከፋዮችን ግብርና ቀረጥ ይወስናል ይሰበስባል በሚወጣ መመሪያ መሠረት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ክፍያዎችንም ይሰበስባል የቀበሌው ገቢ የሚያድግበትን ሁኔታ በማፈላለግ በህግ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል:
   ኀ/ በቀበሌው ክልል ለሚገኙ ክፍት ቦታዎችና የመሬት ይዞታ ሁኔታ የተሟላ መረጃ ይይዛል ይከታተላል በከተማው አስተዳደር (ማዘጋጃ ቤት) ባለቤትነት ስር ያሉ ቤቶች እንዲጠገኑና እንዲታደሱ ያደርጋል፤ ቤቶቹንም ያስተዳድራል ይቆጣጠራል፤
   ነ/ ስለ ቀበሌው ነዋሪዎች ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ መረጃዎችን በማጠናቀር ይይዛል ሲጠየቅም ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል በቀበሌው የመንግስት ፖሊሲና ህጎች እንዲሁም የአስተዳደሩ እንቅስቃሴዎች እንዲታወቁ ያደርጋል::
   ኘ/ በቀበሌው ክልል ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይንከባከባል ይቆጣጠራል::
   አ/ የቀበሌውን ተፈጥሮ ሐብትና አካባቢ ይጠብቃል ይንከባከባል
   ከ/ በቀበሌው ማህበረሰብ መካከል የመቻቻልና የመረዳዳት ባህል እንዲዳብር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል::
   ኸ/ ሴቶችን ከጎጂ ባህልና የፆታ ጥቃት ይከላከላል::
2. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራ ዕቅዶችን የሚነድፈውና አፈጻጸማቸውን የሚከታተለውም ሆነ የሚገመግመው እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል፤ አሠራራቸውም በየቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት የውስጥ መመሪያ ይወሰናል::

### 15. ስለ ቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት አሰያየም እና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌ መስተዳድር ም/ቤት አባላት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሰየማሉ:
2. የመስተዳደር ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ምርጫ ተካሂዶ ተተኪው አካል ሥራውን እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ ይሆናል::

### 16. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሥልጣንና ተግባር

1- የዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር
   ሀ- የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ሆኖ የቀበሌ መስተዳድሩ ሥራ መሪ ነው::

ለ- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው:

1. የቀበሌውን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል
2. የመንግስት ፖሊሲዎች ሕጎች መመሪያዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል
3. የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ልዩልዩ ተቋማትንና በሥሩ የሚገኙትን ንዑስ ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል ይመራል ይቆጣጠራል:
4. የቀበሌው ማኀበራዊ አገልግሎት : የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና ዕቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል:
5. የቀበሌውን ሕግና ሥርዓት እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል:
6. ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና ለመማክርት ጉባኤ ወይም ለተተኪው አካል በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል
7. በክልሉ መስተዳድር ም/ቤትና በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

2- የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር፣

ሀ/ የቀበሌው ምክትል አስተዳደሪ:-

1. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል
2. የቀበሌውን መስተዳድር ም/ቤት (ካቢኔ) አንድ አንአስተባባሪ ሥራ ደርቦ ይሠራል
3. በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ተሰይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል

ለ/ የቀበሌው ምክትል አስተደዳሪ ተጠሪነት ለቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል::

**17. የሌሎች የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት /የሥራ ዘርፍ አስተባባሪዎች/ሥልጣንና ተግባር፤**

የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች በምክር ቤት አባልነታቸው የሚኖራቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በክልል ደረጃ ዋናው መሥሪያ ቤት ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በውክልና የተሰጣቸውን እንደአግባብነቱ ሥራ ላይ ማዋል ሲሆን ተጠሪነታቸውን ለቀበሌው ዋና አስተዳዳሪና በክልል ለሚገኙ ቢሮ ይሆናል:: የያንዳንዱ አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት ዝርዝር በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ይወሰናል::

**18. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት፤**

በክልሉ የሚደራጁት ቀበሌዎች እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ጽ/ቤት ይኖራቸዋል፣ ጽ/ቤቱ በቀበሌ ለሚደራጁትና የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባል ለሆኑ ለሥራ ዘርፍ አስተባባሪዎች ጥምር አገልግሎት ይሰጣል::

## ምዕራፍ ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**19. ስለ ንዑስ ቀበሌዎች መደራጀት:-**

1- በዚህ ደንብ መሠረት በክልሉ የነበሩትን ቀበሌዎች በአዲስ መልክ በ9ኙ የቀበሌ መስተዳድሮች መደራጀታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለልማት ከሚኖረው ጠቀሜታ አንፃር የቀድሞ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች በንዑስ ቀበሌ ደረጃ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ባሉበት ሁኔታ መዋቅራቸውን ይዘው ይቀጥላሉ:: ዝርዝሩ በክልል መስተዳድሩ ምክር ቤት መመሪያ ይወሰናል::

**20. ስለ ቀበሌ ማዕከላት አመራረጥ**

በአዲስ መልክ የሚደራጁ የቀበሌ መስተዳድሮች ማዕከላት አመራረጥ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት/ ካቢኔ/ መመሪያ ይወሰናል::

**21. ስለ ቀበሌዎች የበጀት ምንጭ**

ምንጮቹ:

ሀ. ከመንግሥት የሚመደብ እና

ለ. ከሌሎች አግባብ ካላቸው የፋይናንስ ምንጮች ይሆናል ዝርዝሩ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ይወሰናል::

**22. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚጋጩ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ ውስጥ ለተደነገጉት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም::

**23. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1- በዚህ ደንብ መሠረት አዲሶቹ ቀበሌዎች እስኪደራጁ ድረስ በሥራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል::

2- ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩት ስራዎች በዚህ ደንብ መሠረት በሚመለከተው አካል እንደተጀመሩ ተቆጥረው አፈፃፀማቸው ይቀጥላል::

3- በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 የተመለከተው የቀበሌ መማክርት ጉባኤ የሥራ ዘመን አግባብ ባለው ህግ መሠረት የቀበሌ ምክር ቤቶች እስኪደራጁ ድረስ ብቻ ይሆናል::

**24. መመሪያ ስለማውጣት**

1- በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋሙ የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤቶች ሥልጣንና ተግባራቸውን ሥራ ላይ ለማዋል የሥራ መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ::

**25. የመተባበር ግዴታ**

ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም አካል በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት::

**26 ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከጥቅምት 24/ 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**ሐረር ጥቅምት 24/1997**
**ፉአድ ኢብራሂም**
**የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት**
**ፕሬዝዳንት**

አባድር ማተሚያ ቤት